# የክልል ልዩ ሐይሎችን የማፍረስ ጉዳይ

ሰሞኑን የኢትዮጵያ አስመሳይ ፖለቲከኞች የክልል ልዩ ሐይሎችን ለማፍረስ ሽር ጉድ እያሉ ነው። አስመሳይ ያልኩት ላለፉት 33 ዓመታት የፖለቲካ ሥራ ሲሠሩ ባለማየቴ ነው። ከመጀመሪያው የልዩ ሐይሎች መፈጠር የዚሁ ፈሩን የሳተ ፖለቲካ ውጤት ነው። በትክክለኛው ማሕበራዊ ሳይንስ ፈለግ ፖለቲካ እና ቋንቋ ሕብረተሰብ በሕገ-ፊዚክስ እየተመራ የሚያደርገውን ተፈጥሯዊ ውህደት (integration) ሂደት የሚያግዙ እሴቶች እንጂ አፍራሽ መሠረቶች አይደሉም፤ ሊሆኑም አይችሉም። የሕብረተሰብ የዕድገት ሂደት መዳረሻ መደመር ሳይሆን ውህደት መሆኑን ከ2,400 ዓመታት በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ ከፖለቲካ ሳይንስ አስተሳሰብ ጋር ያስተዋወቀን ሶቅራጥስ ወይም የእሱ ተማሪ (Plato) ተማሪ የነበረው አሪስቶትል ከድምሩ ውህደቱ ይልቃል "The whole is greater than the sum of the parts" ሲል አስተምሮናል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሕብረተሰብ ዕውነትም ውሕደት ከድምር እንደሚልቅ ከሕይወት ገጠመኙ ተረድቷል። ሐቀኛ ተመራማሪ ልሂቃንም ውህደትን ከድምሩ የላቀ የሚያደርገው ከሕዝብ መግባባት፤ መቀራረብ፤ መተማመን፤ መማማር፤ እና መተጋገዝ የሚመነጨው ማሕበራዊ እሴት (synergy) እንደሆነ ደርሰውበታል። የኢትዮጵያን ሕዝብ የቋንቋ ፖለቲካ የዘረፈው እና አሁንም እያሚጠጠ ያለው ይህን አንኳር እሴት ነው።

ወደ ልዩ ሐይሎች ጉዳይ ልመለስ። ልዩ ሐይሎችን ለማፍረስ መጀመሪያ መመለስ ያለበት ከጅምሩ ለምን ተፈጠሩ ወይም ተቋቋሙ የሚለው ጥያቄ ነው። የልዩ ሐይል ጽንሰ ሃሳብ ከቋንቋ ፖለቲካ ጋር የተጣመረ ነው። ልዩ ሐይሎች የግለሰቦች ምኞት የፈጠረው በቋንቋ ላይ የተመሠረተው አደረጃጀት ከተፈጥሯዊው ሕገ-ፊዚክስ ጋር እየተጋጨ በፈጠረው ትርምስ ሳቢያ የቋንቋ ፖለቲካን የሚያራምዱ አስመሳይ ፖለቲከኞች ኢትዮጵያዊያን የነበራቸውን ማዕከላዊ የጋራ ደህንነት ሐይል (security) እያላሉ እያንዳንዱ ማሕበረሰብ እራሱን ከሌሎች እንዲጠብቅ ታስቦ የተፈጠሩ ናቸው። ዋና ዋና ተዋናዮቹ ደግሞ ትሕነግ እና ኦነግ ናቸው። እነዚህ ሁለቱ ከጅምሩ እስካሁን ድረስ ከሚያደርጉት ገጠመኝ የምንገነዘበው ለልዩ ሐይል ያላቸው ድጋፍ ሌሎች ማሕበረሰቦች እንዲጠናከሩ ከመፈለግ ሳይሆን እራስቸው ሌሎችን ለማጥቃት እና ለመቆጣጠር ካላቸው ፍላጎት የመነጨ መሆኑን ነው። እስካሁን ድረስ ለየብቻቸው የበላይ በመሆን ለሕዝብ የማይመጥኑ ተግባሮች ሲያከናውኑ ቆይተው አሁን የጋራ ቁጥጥር ለማድረግ በሁለቱ መካከል አስተማማኝ ግንባር ለመፍጠር እይኳተኑ ይመስላል።

የፖለቲካው ሁኔታ በዚህ ላይ እያለ ቀርቶ ልዩ ሐይሎች እየፈረሱ የማዕከላዊ ሐይልን እንዲቀላቀሉ የሚደረገው (ከተደረገ) በመጀመሪያ እንዲፈጠሩ ምክንያት የሆነው የቋንቋ ክፍፍል ሳይቀረፍ መሆኑ አድራሳቱን አጠያያቂ ያደርገዋል። ክፍፍሉ እያለ የማዕከላዊ ሐይል ማዕከላዊ እንጂ የጋራ ሐይል አይሆንም። ይህንን ሐቅ እስካሁን ካለን ገጠመኝ ተምረናል። በትሕነግ ጊዜ ማዕከላዊ ሐይሉ የትሕነግን ፍላጎት እንጂ የኢትዮጵያዊያንን ትግራዋይኖችን ጨምሮ ፍላጎት ሲያገለግል አልታየም። አሁንም በጊዜው ሥልጣን ላይ ያለው ስብስብ (በተግባር የኦነግ ዓላማ አራማጅ) ማዕከላዊ ሐይሉን እንደፈለገ ሲጠቀምበት እያየን ነው።

ማዕከላዊ ሐይሉን የጋራ ለማድረግ የቋንቋ ክፍፍሉ በሳይንሳዊ አደረጃጀት መተካት እና ሕዝቡ በሕገ-ፊዚክስ መሠረት ሕይወቱን እንዲመራ መጀመሪያ የጋራ እሴት መዳበር መጀመር አለበት። በማሕበረሰቦች መካከል ሳያስፈልግ የተፈጠረው ክፍተት ሲጠፋ እና ሕዝቡ በማዕከላዊ ሐይል ላይ እምነት ሲያድርበት ሐይሉ የጋራ ይሆናል። በዚያን ጊዜ ልዩ ሐይል የሚለው ጽነሰ ሃሳብ ትርጉም ያጣል። ያኔ ልዩ ሐይሎችን ማፍረስ ትክክለኛ እርምጃ ይሆናል።